ኤፌሶን 1



የኤፌሶን ደብዳቤ የመጽሐፍ ርእስ ቢሰጠው 'በክርስቶስ' የሚል ይሆናል!. "በክርስቶስ" የሚለው የጳውሎስ መገለጥ ... እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ላለው ግንኙነት ቁልፍ ነው!! ይህ የመጽሐፍ ቅዱስም ፒን-ኮድ ነው!! የኤፌሶንም ደብዳቤ ቁልፍ ቃል በክርስቶስ የሚል ነው!. በክርስቶስ የተደረግነውን እና ያገኘነውን ይመልከቱ!.

1) እግዚአብሔር በእኛ ሥራ ሳይሆን *በክርስቶስ

በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ ባርኮናል!! (ኤፌሶን 1፥3)

2) እግዚአብሔር ባልነበርንበት ዓለም እና ዘመን *በክርስቶስ መርጦናል!! (ኤፌሶን 1፥4)

3) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ሥራ ልጆቹ አድርጎናል!! (ኤፌሶን 1፥5)

4) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ጸጋን ሰጥቶናል!! (ኤፌሶን 1፥6)

5) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ደም ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ብሏል!! (ኤፌሶን 1፥7) (ኤፌሶን 4፥32)

6) እግዚአብሔር *በክርስቶስ የፈቃዱን ምስጢር አሳታውቆናል!! (ኤፌሶን 1፥9)

7) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ጠቅልሎናል!! (ኤፌሶን 1፥10)

8) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ርስትን ሰጥቶናል!! (ኤፌሶን 1፥11)

9) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ስናምን ... በመንፈሱ አትሞናል!! (ኤፌሶን 1፥13)

10) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ለእኛ ቸርነት አለው!! (ኤፌሶን 2፥6)

11) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ከክርስቶስ ጋር በሰማያዊ ስፍራ አስቀምጦናል!! (ኤፌሶን 2፥7)

12) እግዚአብሔር *በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት አድርጎናል!! (ኤፌሶን 2፥10) (ኤፌሶን 2፥15)

13) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ደም ወደ እርሱ መቅረብን ሰጥቶናል!! (ኤፌሶን 2፥13)

14) እግዚአብሔር *በክርስቶስ አይሁድ እና እኛን በአንድ አካል አድርጎ ታርቆናል፤ እርስበርሳችን አስታርቆናል!! (ወደ ኤፌሶን 2፥16)

15) እግዚአብሔር *በክርስቶስ ሥራ ተቀብሎናል!! (ኤፌሶን 2፥18)

በክርስቶስ የባረከን!.

“#በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።” —ኤፌሶን 1፥3።

እግዚአብሔር እኛን ለመባረክ ከእኛ የተወሰነ ጥረት አልጠየቀም። እኛን ለመባረክ ክርስቶስ በቂ ሆኖ ተገኝቷል። የባረከን በክርስቶስ እንጂ በራሳችን አይደለም።

የባረከን "በሰማያዊ ስፍራዎች እና በመንፈሳዊ በረከቶች ሁሉ" ነው!. ሰማያዊ ስፍራዎቹን ከክርስቶስ ጋር ተቀምጠንባቸዋል!. መንፈሳዊ በረከቶቹን ደግሞ በተረዳነው መጠን እየተጠቀምንባቸው ነው!.

በክርስቶስ የባረከን ይባረክ!.

***

በክርስቶስ መረጠን!.

“ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።” — ኤፌሶን 1፥4።

እግዚአብሔር … በሌለንበት ምርጫ አከናውኗል! ምርጫው ከእርሱ ነው! ምርጫው በክርስቶስ ነው! ምርጫው ወደ እርሱ የመለሰን ነው! እኛ ራሳችንን በማንመርጥበት ምርጫ መርጦናል!

እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ገና ዓለም ሳይፈጠር ነው! ገና ሳንኖር አስቦን አሁን ስንኖር አይረሳንም! በሌለንበት ካሰበልን አሁን እየኖርን አይተወንም!

እኛ በሌለንበት ታቅደናል! አሁን ባለንበት ሁኔታ

ራሳችንን ሳናገኘው በፊት በእርሱ እይታ ፊት ታልመናል! የእርሱ ልብ ወደእኛ ያዘነበለው ገና ወደእርሱ ሳንመጣ ነው! በክርስቶስ ያየን ገና በኢየሱስ ሳናምን ነው! ወዳየው መጥተናል፥ ራእዩ ተሟልቷል!

ሳንኖር ያሰበን እያለን አይረሳንም!
በሌለንበት ያሰበልን ኖረን ለራሳችን አይተወንም!
እናንተ የታሰባችሁ የታሰበላችሁ ናችሁ!

ይቀጥላል!.